# ሰቆቃወ ኤርምያስ

*አስተዋፅኦ*

I. የኢየሩሳሌም ውድመት (1፥1-22)
   (ሀ) የወደመችዋ ከተማ ዝርዝር ሁኔታ (1፥1-7)
   (ለ) የመፍረሰዋ ምክንያት (1፥8-11)
   (ሐ) የሕዝቡ ሥቃይ (1፥12-22)
II. የእግዚአብሔር ቍጣና የኢየሩሳሌም ሐዘን (2፥1-22)
   (ሀ) የእግዚአብሔር ቍጣ በጽዮን ላይ (2፥1-9)
   (ለ) የሕዝቡ ሰቆቃ (2፥10-17)
   (ሐ) የነቢዩ የምሕረት ምልጃ (2፥18-22)
III. የተሠቃዩት የእግዚአብሔር ሕዝብና ተስፋቸው (3፥1-66)
   (ሀ) የተስፋ መቍረጥ ጩኸት (3፥1-18)
   (ለ) የተስፋ ቃላት (3፥40-42)
   (ሐ) የንስሓ ጥሪ (3፥40-42)
   (መ) የነቢዩ መከራ (3፥43-54)
   (ሠ) የነቢዩ ጸሎት (3፥55-66)
IV. የጽዮን ያለፈው፣ የአሁኑና የወደፊቱ ሁኔታ (4፥1-22)
   (ሀ) የጽዮን የቀደመውና የአሁኑ ሁኔታ ንጽጽር (4፥1-12)
   (ለ) የጽዮን ውድመት ምክንያት (4፥13-20)
   (ሐ) የኤዶም ቅጣትና የይሁዳ ተሐድሶ (4፥21-22)
V. የተሐድሶ ጸሎት (5፥1-22)
   (ሀ) የምሕረት አስፈላጊነት (5፥1-15)
   (ለ) የኀጢአት ኑዛዜ (5፥16-17)
   (ሐ) ለተሃድሶ የቀረበ ጥሪ (5፥19-22)

**ጸሓፊ፤** *ኤርምያስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *የጊዜው ሐዘንና የወደፊቱ ተስፋ*

**የተጻፈበት ቀን፤** *586—585 ዓ.ቅ.ክ.*

*ታሪካዊ ዳራ*

የዚህ መጽሐፍ መጠሪያ የተወሰደው በግሪኩና በላቲኑ የብሉይ ኪዳን ትርጒሞች "ሰቆቃወ ኤርምያስ" ተብሎ ከተቀመጠው ንኡስ ርእስ ነው። የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ይህን መጽሐፍ ዩሀግዩግራፋጳ ("ቅዱሳት መጻሕፍት") ተብሎ የሚጠራው የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሦስተኛ ክፍል በማድረግ ከአምስቱ ጥቅልል መጻሕፍት (ከመጽሐፈ ሩት፣ ከመጽሐፈ አስቴር፣ ከመጽሐፈ መክብብና ከማሕልየ መሐልይ ዘሰሎሞን) ጋር ይመድበዋል፤ ከእነዚህ ከአምስቱ ጥቅልል መጻሕፍት ውስጥ እያንዳንዱ በአይሁድ ሥርዐት መሠረት በቅዳሴው ዓመት በተመደበለት ጊዜ ይነበብ ነበር። ይህ መጽሐፍ አይሁድ የኢየሩሳሌም መፍረስ መታሰቢያ በሆነው በአብ ወር (የሐምሌ አጋማሽ አካባቢ) ዘጠነኛ ቀን እንዲነበብ የተወሰነ መጽሐፍ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም (ግሪክ) ዛሬ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች እንደሚታየው "ሰቆቃወ ኤርምያስን ከትንቢተ ኤርምያስ ቀጥሎ አስቀምጦታል።

የሰቆቃወ ኤርምያስ ጸሓፊ ኤርምያስ ለመሆኑ አይሁዳዊውም ሆነ ክርስቲያናዊው ትውፊት ከተስማሙበት ረጅም ጊዜ ዐልፎአል። የዚህን ሐሳብ እውነትነት ከሚያረጋግጡት በርካታ ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፤ (1) ኤርምያስ ሰቆቃው የመጻፍ ልምድ እንዳለው ከ2ዜና 35፥25 መገንዘብ እንችላለን፤ በተጨማሪም ትንቢተ ኤርምያስ ነቢዩ በኢየሩሳሌም ሊመጣ ስላለው ጥፋት ያለቀሰውን ልቅሶ የሚያሳዩ በርካታ ሐሳቦችን ይዞአል (ኤር 7፥29፤ 8፥21፣ 9፥1፡10፡20 ይመ)። (2) ስለ ደረሰው ጥፋት ግልጽ የሆነ ምስል

ማለት ነው። ይህ ግጥምን መነሻ ፊደላቸው ቀኑልቀኑል ሲነበብ ትርጒም በሚሰጡ ሆህያት የመጀመሩ ዘዴ ግጥምን ለማስታወስ ከሚሰጠው ጥቅም በተጨማሪ ሁለት ተግባራትን ለመፈጸም ያስችላል። (1) ሰቆቃዎቹ ከ"ሀ" እስከ "ፐ" (በዕብራይስጡ ከአሌፍ እስከ ታው) ያሉትን ፊደላት ሁሉ አጠቃላይ የያዙ መሆናቸውን ያሳያል። (2) ሰቆቃዎቹን በዚህ መልክ በመጻፍ ነቢዩ ማለቂያ በሌለው ሐዘንና መከራ ውስጥ እንዳይገባ ተገድቦአል፤ የምርኮው ዘመን የሚፈጸምበትና ኢየሩሳሌም እንደ ገና የምትገነባበት ቀን እንደሚመጣ ሁሉ፣ የነቢዩ ሰቆቃም የሚያበቃበት ጊዜ አለ።

## ልዩ ገጽታ

ሰቆቃወ ኤርምያስን ልዩ የሚያደርጉት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ምንም እንኳ ግለሰብንና ማኅበረ ሰብን የሚመለከቱ የሰቆቃ መዝሙሮች በመዝሙረ ዳዊትና በትንቢት መጽሐፎች ቢገኙም፣ ሐዘን የተሞሉ ግጥሞች ያሉበት ይህ መጽሐፍ ብቻ ነው። (2) ሥነ ጽሑፋዊ ውቅሩ ሙሉ በሙሉ ግጥም (ዜማዊ) ሲሆን፣ ከአምስቱ የግጥም ሰቆቃዎች አራቱ መነሻ ፊደላቸው ቀኑልቀኑል ሲነበብ ትርጒም የሚሰጡ ሆህያት የሚጀምሩ ናቸው ("ቅኝት" በሚለው ሥር ያለውን የመጨረሻ አንቀጽ ይመ)። አምስተኛው ግጥም የመጽሐፉን የግጥም ውቅር በመከተል 22 ቍጥሮችን ይዞአል። (3) 2ነገ 25 እና ኤር 52 የኢየሩሳሌምን መፍረስ ታሪካዊ ሁነት የሚገልጹ ቢሆንም፣ መከራ የደረሰባቸውን ሰዎች ስሜትና የልብ ሐሳብ በግልጽ የሚያሳየው ይህ መጽሐፍ ብቻ ነው። (4) በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ታማኝነትና ስለ ድነት በጕልህ ከሚናገሩ አገላለጾች መካከል አንዳንዶቹ በመጽሐፉ አጋማሽ ላይ ሰፍረዋል (3፥21-26)። ሰቆቃወ ኤርምያስ በሰቆቃ ቢጀምርም እንኳ (1፥1-2) አግባብ ባለው መልኩ ተደምድሞ የሚገኘው የንስሓንና የተሓድሶን ተስፋ በሚገልጽ ሐሳብ ነው (5፥16-22)። (5) ይህ መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በየትኛውም ቦታ አልተጠቀሰም፤ ይሁን እንጂ በጥቂት ቦታዎች ላይ በሰያፍ ተጠቍሞአል (ሰቆ 1፥15ን ከራእ 14፥19 ጋር፤ ሰቆ 2፥1ን ከማቴ 5፥35 ጋር፤ ሰቆ 3፥30ን ከማቴ 5፥39 ጋርና ሰቆ 3፥45ን ከ1ቆሮ 4፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

## ሰቆቃወ ኤርምያስ በአዲስ ኪዳን መፈጸሙ

ሰቆቃወ ኤርምያስ በአዲስ ኪዳን የትም ስፍራ ባይጠቀስም እንኳ፣ በክርስቶስ ለሚያምኑት ፋይዳ ያለው እይታ ይሰጣል። እንደ ሮሜ 1፥18—3፥20 ሁሉ እነዚህ አምስት ምዕራፎች ኀጢአት ከባድ መሆኑንና መለኮታዊ ፍርድም የሚያመጣ መሆኑን አማኞች እንዲገነዘቡ ያደርጋሉ። ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖም ከእግዚአብሔር ምሕረትና ርኅራኄ የተነሣ ደኅንነት ከኀጢአታቸው ንስሓ ለሚገቡትና ወደ እግዚአብሔር ለሚመለሱት ድነት ተዘጋጅቶ ያለ መሆኑንም ያሳስቡናል። በተጨማሪም የነቢዩ እንባ ኢየሩሳሌም በሮማውያን የሚደርስባትን ጥፋት ተመልክቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ያነባውን እንባ እንድናስታውስ ያደርገናል (ማቴ 23፥37-38፤ ሉቃ 13፥34-35፤ 19፥41-44)።

## ሰቆቃወ ኤርምያስን ማንበብ

ሙሉውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ አመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በሁለት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤
❑ 1—2 ❑ 3—5

*ማስታወሻ*

እያሉ እናቶቻቸውን ይጠይቃሉ።
13የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ሆይ፤ ስላንቺ
ምን ማለት እችላለሁ?
ከምንስ ጋር አወዳድርሻለሁ? ድንግሊቱ
የጽዮን ልጅ ሆይ፤
አጽናናሽ ዘንድ፣
በምን ልመስልሽ እችላለሁ?
ቍስልሽ እንደ ባሕር ጥልቅ ነው፤
ማንስ ሊፈውስሽ ይችላል?
14ኖን የነቢያቶችሽ ራእይ፣
ሐሰትና ከንቱ ነው፤
ምርኮኛነትሽን ለማስቀረት፣
ኀጢአትሽን አይገልጡም።
የሚሰጡሽም የትንቢት ቃል፣
የሚያሳስትና ከመንገድ የሚያወጣ
ነው።
15ሳምኬት በአጠገብሽ የሚያልፉ ሁሉ፣
እጃቸውን ያጨበጭቡብሻል፤
"የውበት መደምደሚያ፣ የምድር ሁሉ
ደስታ፣
የተባለች ከተማ ይህች ናትን?"
እያሉ ራሳቸውን በመነቅነቅ፣
በኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ላይ
ያሾፋሉ።
16ፌ ጠላቶችሽ ሁሉ በአንድ ላይ፣
አፋቸውን በኀይል ከፈቱ፤
ጥርሳቸውን እያፏጩ አሾፉ፤
እንዲህም አሉ፤ "ውጠናታል፤
የናፈቅነው ጊዜ ይህ ነበር፤
ኖረንም ልናየው በቃን።"
17ዔ እግዚአብሔር ያሰበውን አደረገ፤
ከረዥም ጊዜ በፊት የተናገረውን፣
ቃሉን ፈጸመ፤
ያለ ርኅራኄ አፈረሰሽ፤
ጠላት በሥቃይሽ ላይ እንዲደሰት፣
የጠላትሽንም ቀንድ[a] ከፍ ከፍ
አደረገ።
18ጻዴ የሕዝቡ ልብ፣ ወደ እግዚአብሔር
ጮኸ።
የጽዮን ሴት ልጅ ቅጥር ሆይ፤
ቀንና ሌሊት፣
እንባሽ እንደ ወንዝ ይፍሰስ፤
ለራስሽ ዕረፍትን አትስጪ፣
ዐይኖችሽ ከማንባት አያቋርጡ።
19ቆፍ የሌሊቱ ሰዓት ሲጀምር፣
ተነሺ፤ በሌሊት ጩኺ፤
በእግዚአብሔር ፊት፣
ልብሽን እንደ ውሃ አፍስሺ፤
በየመንገዱ ዳር ላይ፣ በራብ ስለወደቁት፣
ስለ ልጆችሽ ሕይወት፣ እጆችሽን
ወደ እርሱ አንሺ።
20ሬስ እቤቱ እግዚአብሔር ሆይ እይ፤
ተመልከትም፤
በማን ላይ እንዲህ አድርገህ
ታውቃለህ?
በውኑ እናቶች ሕፃኖቻቸውን፣
ተንከባክበው ያሳደጓቸውን ልጆች
ይብሉን?
ካህኑና ነቢዩስ፣
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ
ይገደሉን?
21ሳን በየመንገዱ ዐቧራ ላይ፣
ወጣትና ሽማግሌ በአንድነት
ወደቁ፤
ወይዛዝርቴና ጐበዛዝቴ፣
በሰይፍ ተገደሉ፤
በቍጣህ ቀን ገደልሃቸው፤
ያለ ርኅራኄም ዐረድሃቸው።
22ታው "በበዓል ቀን ለግብዣ
እንደምትጠራ፤
ሽብርን ከየአቅጣጫው በእኔ ላይ
ጠራህ፤
በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን፣
ማንም አላመለጠም ወይም
አልተረፈም፤
የተንከባከብኳቸውንና ያሳደግኋቸውን፣
ጠላቴ አጠፋብኝ።"

3 አሌፍ[b] በቍጣው በትር፣
መከራ ያየ ሰው እኔ ነኝ።
2ከፊቱ አስወጣኝ፤
በብርሃን ሳይሆን በጨለማ እንድሄድ
አደረገኝ።
3በእርግጥ ቀኑን ሁሉ በመደጋገም፣

2፥13 2ነገ19፥21፤ ኢሳ1፥6፤ 37፥22፤ ኤር14፥17፤ 30፥12-15፤ ሰቆ1፥12
2፥14 ኤር2፥8፤ 8፥11፤ 20፥6፤ 23፥25-32፡33-40፤ 28፥15፤ 29፥9፤ ሕዝ13፥3፤ 22፥28
2፥15 ዘኍ24፥10፤ ዘዳ28፥37፤ ኢዮ16፥4፤ መዝ45፥11፤ 48፥2፤ 50፥2፤ ኢሳ28፥22፤ ኤር19፥8፤ ሰቆ1፥21፤ ሕዝ16፥14፤ 25፥6፤ ናሆ3፥19
2፥16 ኢዮ16፥9፤ መዝ22፥13፤ 35፥25፤ ሰቆ3፥46፤ ሕዝ36፥3፤ ሚክ4፥11
2፥17 ቍ2፤ ዘዳ28፥15-45፤ መዝ22፥17፤ 89፥42፤ ኢሳ44፥26፤ ኤር39፥16፤ ሰቆ1፥5፤ ሕዝ5፥11፤ 7፥9፤ 8፥18፤ ዘካ1፥6
2፥18 ቍ8፤ መዝ119፥145፤ ኤር9፥1፤ ሰቆ1፥16፤ 3፥49
2፥19 ቍ11፤ 1ሳሙ1፥15፤ መዝ28፥2፤ ኢሳ26፥9፤ 51፥20
2፥20 ዘዳ28፥53፤ መዝ78፥64፤ ኤር14፥15፤ 23፥11-12፤ 19፥9፤ ሰቆ1፥19፤ 4፥10፤ ሕዝ5፥10
2፥21 ዘዳ32፥25፤ 2ዜና36፥17፤ መዝ78፥62-63፤ ኤር6፥11፤ 13፥14፤ ሰቆ3፥43፤ ዘካ11፥6
2፥22 ኢዮ27፥14፤ መዝ31፥13፤ ኤር11፥11፤ 20፥10፤ ሆሴ9፥13
3፥1 ኢዮ19፥21፤ መዝ88፥7፤ ኤር15፥17-18
3፥2 ኢዮ19፥8፤ መዝ82፥5፤ ኤር4፥23 3፥3 መዝ38፥2፤ ኢሳ5፥25

[a] 2፥17 ቀንድ በዚህ ቦታ ብርታትን ያመለክታል
[b] 3፥1 የዚህ ምዕራፍ እያንዳንዱ አንጓ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምር ሲሆን በእያንዳንዱ አንጓ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች በአንድ ዐይነት ፊደል ይጀምራሉ።

*በብሉይ ኪዳን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

2፥14 **ኀጢአትሽን አይገልጡም፤** የሐሰተኛ ነቢይ አንዱ ምልክት በሕዝቡ መካከል ያለውን ኀጢአት በቃሉም ሆነ በራእዩ አለመግለጡ ነው (በገጽ 1009 ላይ፣ «*ነቢይ በብሉይ ኪዳን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የተኵረት ጽሑፍ ይመ)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያሉ፣ የመንፈስ ቅዱስን የመውቀስ ተግባር በማግለጽ (ዮሐ 16፥8-11) ስለ ኀጢአት የማይገሥጹ ሐሰተኛ አገልጋዮች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። በተቃራኒው፣ የተቀደሰ ሕይወት እየኖሩ ክርስቶስ እንዳደረገው ሁሉ በጉባኤ መካከል የሚታየውን ዓለማዊነትና ኀጢአት ከልባቸው በመቃወም የሚናገሩ (ራእ 2-3 ይመ)፣ የአምላካቸው ታማኝ አገልጋይ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

2፥18 **እንባሽ ... ይፍሰስ፤** እግዚአብሔር የትሩፋኑን የምልጃ ጩኸት እንደሚሰማ ተስፋ በማድረግ፣ ኢ ርምያስ ታማኝ እንዲጸልዩ፣ እንዲያለቅሱና ንስሓ እንዲገቡ ጥሪ ያቀርባል (ከቍ 19 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥1 **ሰው እኔ ነኝ፤** ምዕ 3 ላይ ጥቃት ደርሶበት የምናየው የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር የቅጣት በትር ሥር እንዳለ ሰው ሆኖ ይታይ እንጂ የመታደስ ተስፋ አለው። እንዲህ ያለ ሰው የእግዚአብሔር ፍቅርና ርዳታ ንስሓ ለሚገቡና ጌታን በጽናት ለሚጠብቁ እንደሚመጣላቸው ያስባል (ቍ 22-27)።

እጁን በላዬ ላይ መለሰ።
4ቤት እርሱ ሥጋዬንና ቈዳዬን አስረጀ፤
ዐጥንቶቼንም ሰባበረ።
5በምሬትና በድካም፣
ቅጥር ሠራብኝ፤ ዙሪያዬንም
ከበበኝ።
6ከሞቱ ብዙ ጊዜ እንደሆናቸው፣
በጨለማ እንድኖር አደረገኝ።
7ጋሜል በቅጥር ውስጥ ዘጋብኝ፤ ስለዚህ
ማምለጥ አልቻልሁም፤
የእስር ሰንሰለቴንም አከበደብኝ።
8ርዳታ ፈልጌ ብጣራና ብጮኽ እንኳ፣
ጸሎቴን መስማት አልፈለገም።
9መንገዴን በተጠረቡ ድንጋዮች ዘጋ፤
ጐዳናዬንም አጣመመ።
10ዳሌጥ አሸምቆ እንደ ተኛ ድብ፣
እንደ አደባም አንበሳ፣
11ከመንገድ ጐትቶ አስወጣኝ፤
ቈራረጠኝም፤
ያለ ረዳትም ተወኝ።
12ቀስቱን ገተረ፤
ለፍላጻዎቹም ዒላማ አደረገኝ።
13ሄ ፍላጻዎችን ከሰገባው አውጥቶ፣
ልቤን ወጋው።
14ለሕዝቤ ሁሉ ማላገጫ ሆንሁኝ፤
ቀኑን ሙሉ በመሣለቅ
ያዜሙብኛል።
15መራራ ሥር አበላኝ፤
ሐሞትም አጠገበኝ።
16ዋው ጥርሴን በድንጋይ ሰበረ፤
በትቢያ ውስጥ ረጋገጠኝ።
17ነፍሴ ሰላምን አጣች፤
ደስታ ምን እንደ ሆነ ረሳሁ።
18ስለዚህ፣ "ክብሬ፣
ከእግዚአብሔርም ተስፋ ያደረግሁት
ሁሉ ሄዶአል" አልሁ።
19ዛይ የጒንቀቴንና የመንከራተቴን፣
ምሬትንና ሐሞትን አስባለሁ።
20ዘወትር አስበዋለሁ፤
ነፍሴም በውስጤ ተዋርዳለች።
21ሆኖም ይህን አስባለሁ
እንግዲያስ ተስፋ አለኝ፤
22ሔት ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ታላቅ
ፍቅር የተነሣ ነው፤
ርኅራኄው አያልቅምና።
23ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤
ታማኝነትህም ብዙ ነው።
24ራሴን እንዲህ አልሁት፤ "እግዚአብሔር
ዕድል ፈንታዬ ነው፤
ስለዚህ ተስፋ አደርገዋለሁ።
25ጤት እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት፣
ለሚፈልገውም ሰው እግዚአብሔር
መልካም ነው።
26ሰው የእግዚአብሔርን ማዳን፣
ዝም ብሎ ተስፋ ቢያደርግ መልካም
ነው።
27ሰው በወጣትነቱ፣
ቀንበር ቢሸከም መልካም ነው።
28ዮድ ብቻውን ዝም ብሎ ይቀመጥ፤
እግዚአብሔር አሸክሞታልና።
29ፊቱን በዐቧራ ውስጥ ይቅበር፤
ተስፋ ሊኖር ይችላልና።
30ጒንጩን ለሚመታው ሰው ይስጥ፤
ውርደትንም ይጥገብ።
31ካፍ እግዚአብሔር ሰውን፣
ለዘላለም አይጥልምና፤
32መከራን ቢያመጣ እንኳ ይራራል፤
ታላቅ ፍቅሩ አይለወጥምና
33ሆን ብሎ ችግርን፣
ወይም መከራን በሰው ልጆች ላይ
አያመጣምና።
34ላሜድ የምድሪቱ እስረኞች ሁሉ፣
በእግር ሲረገጡ፣
35በልዑል ፊት፣
ሰው መብቱ ሲነፈገው፣
36ሰው ፍትሕ ሲጓደልበት፣
ጌታ እንዲህ ዐይነቱን ነገር
አያይምን?

3፥4 ኢዮ30፥30፤ መዝ51፥8፤ ኢሳ38፥13፤ ኤር50፥17፤ ሰቆ4፥8
3፥5 ቍ19፤ ኤር23፥15
3፥6 መዝ88፥5-6፤ 143፥3፤ ኢሳ59፥10
3፥7 ኢዮ3፥23፤ ኤር40፥4
3፥8 ቍ44፤ ዘዳ1፥45፤ ኢዮ30፥20፤ መዝ5፥2፤ 22፥2
3፥9 ኢዮ9፥24፤ 19፥8፤ ኢሳ63፥17፤ ሆሴ2፥6
3፥10 ኢዮ10፥16፤ ሆሴ13፥8፤ አሞ5፥18-19
3፥11 ሆሴ6፥1
3፥12 ኢዮ7፥20፤ 16፥12፤ መዝ7፥12-13፤ 38፥2፤ ሰቆ2፥4
3፥13 ኢዮ6፥4፤ 16፥13
3፥14 ዘፍ38፥23፤ ኢዮ17፥2፤ 30፥9፤ መዝ22፥6-7፤ ኤር20፥7
3፥15 ቍ19፤ ኤር9፥15
3፥16 መዝ7፥5፤ ምሳ20፥17
3፥18 ቍ54፤ ኢዮ 17፥15
3፥19 ቍ5፡15
3፥20 መዝ42፥5፡11፤ 43፥5
3፥22 ዘዐ78፥38፤ 130፥7፤ 103፥11፤ ኢዮ 34፥15፤ ሆሴ11፥9
3፥23 ዘዐ34፥6፤ ሶፎ3፥5
3፥24 መዝ119፥57
3፥25 መዝ33፥18፤ ኢሳ25፥9፤ 30፥18 3፥26 መዝ37፥7፤ 40፥1፤ ኢሳ7፥4 3፥28 ኤር15፥17፤ ሰቆ2፥10 3፥29 ኢዮ2፥8፤ ኤር31፥17 3፥30 ኢዮ16፥10፤ ኢሳ50፥6፤ ሚክ5፥1 3፥31 መዝ94፥14፤ ኢሳ54፥7 3፥32 መዝ78፥38፤ 106፥43-45፤ ሆሴ11፥8፤ ናሆ1፥12 3፥33 ኢዮ37፥23፤ ኤር31፥20፤ ሕዝ18፥23፤ 33፥11 3፥35 ዘፍ14፥18፡19፡20፡22 3፥36 መዝ140፥12፤ ምሳ17፥15፤ ኤር22፥3፤ ዕን1፥13

**3፥8 ጸሎቴን መስማት አልፈለገም፤** ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው ሰዎች በኀጢአትና በርኵሰት ከመኖራቸው የተነሣ ከሚደርስባቸው የከፋ ነገር መካከል አንደኛው እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ለመስማት አለመፈለጉ ነው (ከቍ 44፤ ከመዝ 18፥41፤ ከምሳ 1፥28፤ ከኤር 7፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 528 ላይ፣ "*መልስ የሚያስገኝ ጸሎት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥21-33 እንግዲያስ ተስፋ አለኝ፤** ኤርምያስ ሁሉም ጨርሶ እንዳልጠፋ ሕዝቡ ያውቁ ዘንድ ፈለገ። ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ ተስፋ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ (1) የእግዚአብሔር ቍጣ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሲቆይ ፍቅሩ ግን አያቋርጥም (ቍ 22)። እግዚአብሔር ይሁዳን በቃል ኪዳን ሕዝብነታቸው አልተዋቸውም፤ አሁንም ቢሆን ለእነርሱ አላማ አለው። (2) እግዚአብሔር በትሕትናና በንስሓ ለሚጠብቁት በጎና መሓሪ ነው (ቍ 24-27)። (3) እግዚአብሔር ቅጣቱ ግቡን ሲመታ መከራ በሚደርስባቸው ላይ ርኅራኄውን ማሳየት ይሻል (ቍ 28-33፤ የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

**3፥27-33 ቀንበር ቢሸከም፤** እግዚአብሔር በእርሱ ላይ በሚያምኑት ሕይወት ላይ ጠቃሚ የሆነውንና የሚያንጻ ሥራውን ለመሥራት ሲል አንዳንድ ጊዜ መከራን ያመጣል። በእንዲህ ዓይነት መከራ ውስጥ የሚያልፉ ኀጢአታቸውን ሊናዘዙ፣ ይቅርታን ሊለምኑና ለይቅርታና ለመታደስ በእግዚአብሔር ሊታመኑ ይገባል።

**3፥33 ሆን ብሎ ችግርን … አያመጣምና፤** እግዚአብሔር ሰዎችን በኀጢአታቸው ምክንያት ሲቀጣቸው ደስ አይሰኝም፤ የሚቀጣቸው በዓለም ላይ ግብረገባዊ ሥርዐት እንዲሰፍን ነው። እግዚአብሔር መከራ ሲያመጣ ዋነኛ ዐላማው ሰዎችን ወደ ራሱ ለመመለስ ነው (ሕዝ 18፥23፡32፤ ሆሴ 11፥8፤ 2ጴጥ 3፥9 ይመ)።

2 ርስታችን ለመጻተኞች፣
ቤቶቻችን ለባዕዳን ዐልፈው ተሰጡ።
3 ወላጅ አልባና አባት የሌላቸው ሆንን፤
እናቶቻችን እንደ መበለቶች ሆኑ።
4 ለምንጠጣው ውሃ መክፈል ነበረብን፤
ዕንጨታችንንም የምናገኘው በግዢ
ነበር።
5 የሚያሳድዱን ከተረከዞቻችን ሥር
ናቸው፤
ተጨንቀናል ዕረፍትም አጥተናል።
6 እንጀራ እንጠግብ ዘንድ፣
ለአሦርና ለግብፅ እጃችንን ሰጠን።
7 አባቶቻችን ኀጢአት ሠርተው አለፉ፤
እኛም የእነርሱን ቅጣት ተሸከምን።
8 ባሮች ሠልጥነውብናል፤
ከእጃቸው ነጻ የሚያወጣን ማንም
የለም።
9 በምድረ በዳ ካለው ሰይፍ የተነሣ፣
በሕይወታችን ተወራርደን እንጀራ
አገኘን።
10 ቈዳችን እንደ ምድጃ ጠቍሮአል፤
በራብም ተቃጥሎአል።
11 ሴቶች በጽዮን፣
ደናግል በይሁዳ ከተሞች ተደፈሩ።
12 መሳፍንት በእነርሱ እጅ ተሰቀሉ፤
ሽማግሌዎችም አልተከበሩም።
13 ጕልማሶች ወፍጮ እንዲፈጩ ተገደዱ፤
ወንዶች ልጆች በዕንጨት ሸክም
ተንገዳገዱ።

5፥2 መዝ79፥1፤ 109፥11፤ ኤር17፥4፤ ሶፎ1፥13 5፥3 ዘፀ22፥24፤ ኤር15፥8፤ 18፥21 5፥4 ኢሳ3፥1፤ ኢሳ55፥1፤ ሕዝ4፥16-17 5፥5 ኢሱ1፥13፤ ነህ9፥37፤ ኢሳ47፥6 5፥6 ኤር2፥36፤ ሆሴ5፥13፤ 7፥11፤ 9፥3 5፥7 ኤር14፥20፤ 16፥12፤ 31፥29 5፥8 ነህ5፥15፤ ዘካ11፥6 5፥10 ኢዮ30፥30፤ ሰቆ4፥8-9 5፥11 ዘዳ34፥29፤ ዘካ14፥2 5፥12 ዘሌ19፥32፤ ሰቆ2፥6፤ 4፥16 5፥14 ኢሳ24፥8፤ ኤር7፥34 5፥15 ኤር25፥10፤ አሞ8፥10 5፥16 ኢዮ19፥9፤ መዝ89፥39፤ ኢሳ3፥11፤ ኤር13፥18፤ 14፥20 5፥17 ኢዮ16፥8፤ መዝ6፥7፤

14 ሽማግሌዎች ከከተማዪቱ በር ሄደዋል፤
ጕልማሶች ዝማሬያቸውን
አቁመዋል።
15 ደስታ ከልባችን ጠፍቶአል፤
ጭፈራችን ወደ ልቅሶ ተለውጦአል።
16 አክሊላችን ከራሳችን ላይ ወድቆአል፤
ወዮልን፤ ኀጢአት ሠርተናልና!
17 ከዚህ የተነሣ ልባችን ደከመ፤
ከእነዚህ የተነሣም ዐይናችን ፈዘዘ፤
18 ባዶዋን የቀረችው የጽዮን ተራራ፣
የቀበሮዎች መፈንጫ ሆናለችና።
19 አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
ለዘላለም ትገዛለህ፤
ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራል።
20 ስለምን ፈጽመህ ትረሳናለህ?
ስለምንስ ለረዥም ጊዜ ትተወናለህ?
21 እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ
መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን፤
ዘመናችንን እንደ ቀድሞው አድስ፤
22 ፈጽመህ ካልጣልኸን፣
ከመጠን በላይ ካልተቈጣኸን።

5፥17 ኢሳ1፥5፤ ኤር8፥18 5፥18 መዝ74፥2-3፤ ኢሳ27፥10፤ ሚክ3፥12 5፥19 1ዜና16፥31፤ መዝ45፥6፤ 102፥12፡24-27 5፥20 መዝ13፥1፤ 44፥24፤ 71፥11 5፥21 መዝ80፥3፤ ኢሳ60፥20-22 5፥22 መዝ53፥5፤ 60፥1-2፤ ኢሳ64፥9፤ ኤር6፥30

ሊያያቸው እንደሚችል ኤርምያስ የገለጸበት የምልጃ ጸሎት ነው::
**5፥2-18 ለባዕዳን ዐልፈው ተሰጡ፤** ጸሓፊው ምርኮኞቹ የነበሩበትን አስከፊ አካላዊና አእምሮአዊ ሁኔታ በግልጽ አስቀምጦአል:: ስደትና ፍርሃት የሕዝቡ የዘወትር ተመክሮዎች ነበሩ::

**5፥21-22 ወደ አንተ መልሰን፤** ሰቆቃወ ኤርምያስ የሚደመደመው የእግዚአብሔር ምሕረት እንደሚመጣ ተስፋ በሚያሳይ ጸሎት ነው:: መጽሐፉ በእግዚአብሔ ር የቅጣት እጅ ብንሆንም፣ በአስከፊ ገጠመኝም ውስጥ ብንገኝ እግዚአብሔርን እንድንጠራ ያስተምረናል::